# ከቅኝ ግዛት አመለካከት ያልተላቀቀው ጋዜጠኛ

አዲስ ቶልቻ 05/24/13

በኢትዮጵያ ታሪክ ሃሳብን የመግለፅ ነፃነትና ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት መገለጫ የሆነው የፕሬስ ነፃነት ለመጀመሪያ ጊዜ የተከበረው የወታደራዊ ደርግ የመንግስት ስርዓት ከወደቀ በኋላ መሆኑ ይታወቃል ። የደርግ መንገስትን ውድቀት ተከትሎ በአገር ውስጥና በውጭ ስርዓቱን ሲታገሉ የነበሩ ወገኖች የመሰረቱት የሽግግር መንግስት በ1984 ዓ.ም ለአገሪቱ የመጀመሪያ የሆነውን የፕሬስ ነፃነት አዋጅ አወጣ።

ይህን ተከትሎ በአገሪቱ ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የግል ጋዜጦችና መፅሄቶች ታትመው መሰራጨት ጀመሩ። ይሁን እንጂ አብዛኞቹ የግል ፕሬስ ውጤቶች የተመሰረቱት የመገናኛ ብዙሃንን ለፕሮፓጋንዳ ዓላማ የመጠቀም ልምድና አቅም ባላቸው የቀድሞው ስርዓት አምባገነን ፓርቲ -ኢሰፓ አባላትና ካድሬዎች በመሆኑ ብልጭ ያለወን ዴሞክራሲና ሰላም ከማስቀጠል ይልቅ ለመቀልበስ አላማ የዋሉ ነበሩ።

እነዚህ ቀልባሽ የፕሬስ ውጤቶች እያደረ በአንጻራዊነት የተሻለ ሙያዊና ነፃ ሊባሉ የሚችሉ ጋዜጦች መፈጠር ሲጀምሩ ህዝቡ እየተፋቸው ከህትመት ውጭ ሆኑ፡፡ በ1984ና 85 ዓ.ም እንደነበሩት አይነት ጦር አውርድ የፈጠራ ወሬ የሚነዙ፣ ጅራፍ እሳት፣ ክብሪት፣ መብረቅ፣ ሳተናው … የተባሉ ጋዜጦች አሁን ታትመው ቢሰራጩ ማንም ዞር ብሎ አያያቸውም። ይህ ጋዜጦቹ ከስርጭት ውጭ የሆኑት በህዝቡ ተተፍተው መሆኑን በግልፅ ያሳያል።

የፕሬስ ነጻነት መከበር ያስገኘላቸውን ዕድል ተጠቅመው ይህን መብት የሰጣቸውን ህገመንግስታዊ ስርዓት ለመናድ ዓልመው ሲንቀሳቀሱ የነበሩት የግል የፕሬስ ውጤቶች የ1997 ምርጫን አስታከው ያልተጨበጠ ምክንያት በማቅረብ ስልጣን በኃይል ለመመንተፍ የተቀሰቀሰውን ቡድን ሁከት በመለኮስ ረገድ ከፍተኛ ድረሻ ነበራቸው።

በቅርቡ በኢትዮጵያ ሚዲያ ችግሮች ዙሪያ ከግሉ ሚዲያ ባለቤቶችና ከመንግስት ሚዲያ የስራ ኃላፊዎች ጋር በተካሄደ ውይይት ላይ፣ የኢትዮጵያን የግል ሚዲያ አካሄድ አስመልክቶ የመንግስት የኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ በረከት ስምኦን ባደረጉት

ንግግር “የቆየው ሚዲያ ህገመንግስታዊ ስርዓቱን ለመናድ የሚፈልግ ነበር፤ ይህ መንግስትንና የአገራችንን ዴሞክራሲ አስከፍሏቸዋል” ብለዋል፡፡

ያም ሆነ ይህ የነባሩ የግል የመገናኛ ብዙሃን አካሄድ ሙሉ በሙሉ ተቀይሯል ማለት ባይቻልም፣ ከዚህ አካሄድ ነጻ የሆኑና በአገራችን አጭር የፕሬስ ታሪክ ውስጥ አንጋፋ ለመባል የበቁ ጋዜጦች ተፈጥረዋል። ከአምስት አመት ወዲህ ደግሞ የግል ኤፍ ኤም የሬድዮ ስርጭት አገልግሎቶች ፕሬሱን ተቀላቅለዋል።

ይሁን እንጂ አንዳንድ ቡድኖችና ግለሰቦች “በኢትዮጵያ የፕሬስ ነፃነት እየቀጨጨ ነው” የሚል የከረረ እችት ሲሰነዝሩ ይስተዋላሉ። አብዛኞቹ ትችቶች በስራ ላይ ያሉትን የፕሬስ ውጤቶች መነሻ የሚያደርጉ ሳይሆኑ፣ በተለይ በወንጀል ተከሰው ጥፋተኝነታቸው በማስረጃ ተረጋግጦ ቅጣት የተወሰነባቸውንና በማረሚያ ቤት የሚገኙ ጥቂት ጋዜጠኞች ላይ የተንጠለጠሉ ናቸው።

በዚህ ጉዳይ ላይ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ነን የሚሉ ድርጅቶች ተደጋጋሚ መግለጫና ሪፖርት ሲያወጡ፣ የዛኑ ያህል መንግስትና ሌሎች ዜጎች ምላሽ ትክክል አይደላችሁም እያሉ አጸፋዊ ምላሽ ሲሰጡ ቆይተዋል። ለዚህ ፅሁፍ አላማ በኢትዮጲያ አዲስ አበባ በመከበር ላይ ያለውን የአፍሪካ ህበረት 50ኛ ዓመት በአል አስታኮ የተሰነዘረ አንድ አስተያየት ላይ አተኩራለሁ፡፡

ይህም ከዚህ ቀደም በህዝብ ተወካዮች ምክርቤት በሽብርተኘንት ከተፈረጀው የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃነተ ግነባር - ኦበነግ ጋር በህገወጥ መንገድ ወደአገር ውስጥ በመግባቱና የአሸባሪዎች ተባባሪ በመሆኑ ክስ ተመስርቶበተ ቅጣት ከተወሰነበት በኋላ በይቅርታ ነፃ የተለቀቀው ማረቲን ሹብዬ የተባለው ስዊድናዊ ጋዜጠኛ የሰጠው መግለጫ ነው፡፡

ሹብዬ ከጠበቃው ጋር ሆኖ አወጣው የተባለውን መግለጫ አስመልክቶ የተናገረውን የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ የአማርኛ ፕሮግራም በሰሞኑ ስርጭቱ አቅረቦት ነበር።

ጥፋተኛነቱን አምኖ የኢትዮጵያ ህዝብና መንገስትን ይቅርታ ጠይቆ በነፃ የተለቀቀው ሹብዬ፣ የአፍሪካ የአልቃይዳ ክንፍ የሆነውን አልሸባብ ተልዕኮ በሚያስፈጽመው ኦብነግ እየተመራ በሕገወጥ መንገድ የኢተዮጵያን ድንበር ተሻገሮ መግባቱ ጥፋት ያልሆነ ይመስል፣ ራሱን የሰብአዊ መብት ተሟጋች አድርጎ አቅርቧል፡፡

ሹብዬ በኢትዮጵያ ሕዝብና መንግስት ስር ወድቆ ይቅርታ መጠየቁንም የዘነጋው ይመስላል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የፈጸመውን ወንጀልና የሰጠውን ይቅርታ አይረሳም፡፡ ያም ሆነ ይህ አሁን ሹብዬ መንግስትን በመቃወም በጽንፈኛ አቋማቸው ከሚታወቁት ኢትዮጵያውያንና ትወልደ ኢትዮጵያውያን ተርታ ተሰልፏል። በአጭሩ ወንዱ እና ጎሜዝ ሆኗል፡፡

ሹብዬ ለቪኦኤ የሰጠውን ማብራሪያ የጀመረው ኢትዮጵያ ውስጥ ማረሚያ ቤት እያለ አጋጠመኝ ያለውን ሁኔታ በማውራት ነበር። ይህን አስመልክቶ " በማረሚያ ቤት እያለሁ የአፍሪካ  ህብረት ስብሰባ ከመካሄዱ በፊት የነበሩትን ቀናት አስታውሳለሁ። ከምሽቱ 2 ሰዓት እስረኞች ተሰብስበን የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንን እንድንመለከት <u>እንገደድና</u> ምዕራባውያን ዲፕሎማቶች ከኢትዮጵያውያን ፖለቲከኞች ጋር ሲንሾካሾኩ እናይ ነበር።" ብሏል።

ልብ በሉ "የኢትዮጵያን ቴሌቪዥን እንድንመለከት እንገደድ ነበር" ነው ያለው፡፡ ሸብዬ ይህን ያለው  ወደ ዋናው ዓላማው ለመንደርደር እንዲመቸው ነው። እርግጥ ነው ማረሚያ ቤቶች ውስጥ ቴሌቭዥኖች አሉ። ይሁን እንጂ ታራሚዎች የተወሰኑ ፕሮግራሞች ተለየተው እንዲመለከቱ አይገደዱም። ይህ በማረሚያ ቤት ውስጥ ተደርጎ አያውቅም፡፡ የሸብዬ ውሸት የሚጀምረው ከዚህ ነው።

"ተገድጄ እመለከተው ነበረ" ባለው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን "የአፍሪካ ህበረት ስብሰባ ሲካሄድ የኢትዮጵያ ፖለቲከኞች ከምእራባውያን ዲፕሎማቶች ጋር ሲንሾካሾኩ እናያለን" ብሎናል። የአፍሪካ ህበረት ስብሰባ ዋነኞቹ ተሳታፊዎች የአፍሪካ መሪዎች ሆነው ሳሉ፣ ለሹብዬ ግን የሚታዩት ተጋባዥ ሆነው የተገኙ ጥቂት ምዕራባውያን ዲፕሎማቶች ናቸው፡፡ በአፍሪካውያን በተሞላውና ምዕራባውያን የተለየ ስፍራ ላይ በሚቀመጡበት ስብሰባ ላይ የምዕራባውያኑ ዲፕሎማቶችና የኢትዮጲያ ፖለቲከኞች መንሾካሾክ እንደአጋጣሚ ሊሆን የሚችል እንጂ የአፍሪካ ሕብረት ስብሰባው ዋና መገለጫ አይደለም። ሲንሾካሾኩ ቢታዩም የሚታዩት አፍሪካውያኑ ምሪዎች ናቸው፡፡

ሹብዬ ይህን ሁሉ ድራማ መፍጠር ያስፈለገው ምዕራባውያኑ ዲፕሎማቶችና ኢትዮጵያኑ ፖለቲከኞች ሲንሾካሾኩ በአውሮፓዊነቱ ኢትዮጵያውያን የማረሚያ ቤት ጓደኞቹ ጠየቁኝ ያለውን የፈጠራ ጥያቄ ለማንሳት ነው። "ይሄኔ ጋደኞቼ ምዕራባውያን  ስለሰብአዊ መብት

ግድ የላቸውም ማለት ነው? ለእነሱ የፕሬስ ነፃነት አስፈላጊ አይደለም? እዚህ መጥተው ጋዜጠኞች ከሚያስር መንግስት ጋር ኮክቴል ፓርቲ ላይ ይገኛሉ?" እያሉ በጥያቄ ያጣድፉኛል ብሏል፡፡ በሌላ አነጋገር "የኢትዮጵያ መንግስት ምን ማድረግና ምን ማድረግ እንደሌለበት ለምን አይነገሯቸውም እያሉኝ ነው" ባይ ነው፡፡

ሹብዬ ወንጀል ሰርተው በማረሚያ ቤት የሚገኙተን ታራሚዎች በሙሉ "ሰብአዊ መብታቸው የተጣሱ ናቸው" ለማለት ያዳዳዋል። ጓደኞቹ የሚላቸው ስራቸው ጋዜጠኝነት የሆኑና እንደእርሱ በሽብር ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው ቅጣት የተወሰነባቸውንም ሰዎች " የሰበአዊ መብታቸው ተጥሷል" እያለ ነው።

በርካታ የግል የፕሬስ ውጤቶችና በእነዚህ የፕሬስ ውጤቶች ላይ  የሚሰሩ ጋዜጦች ባለባት ኢትዮጵያ በሽብር ወንጀል ተጠርጥረው ቅጣት የተወሰነባቸውን ሁለት ሶስት ስራቸው ጋዜጠኞነት የሆነና የታሰሩብትን ጉዳይ ልዩ ትርጓሜ ለማሰጠት ጋዜጠኞች ሳይሆኑ ጋዜጠኛ የተባሉ ሌሎች አንድ ሁለት ግለሰቦችን እያስታወሱ "በኢትዮጵያ ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት፣ የፕሬስ ነፃነት ሊሞት ተቃርቧል።" የሚሉ ጉዳዩን ለፖለቲካ ዓላማ ማሳኪያነት መጠቀም የሚፈልጉ ወገኖች መኖራቸው አዲስ ነገር አይደለም፡፡

ከዚህ በመነሳት ምእራባውያን በኢዮጵያ መንግስት ላይ ጫና እንዲያሳድሩ ሲለማመኑ የቆዩ ቡድኖችና ግለሰቦችም አሉ፡፡ ሹብዬም ስለምእራባውያኑ ዲፕሎማቶች ያነሳው ለዚሁ ዓላማ ነው፡፡  ሹብዬ ምዕራባውያኑን ዲፕሎማቶች በኢትዮጵያ ላይ ያሻቸውን የማድረግ ኃይል እንዳላቸው ነው የሚያስበው። ስለምዕራባውያን ዲፕሎማቶች ያነሳው ለዚህ ነው።

ይህ "ምዕራባውያንን በኢትዮጵያና በአፍሪካ ላይ የፈለጉትን የማድረግ ኃይል አላቸው" የሚለው የሹብዬ ግምት ከቅኝ ገዢነት አመለካከት የመነጨ ንቀት ያለው መሆኑን ያንፀባርቃል። ኢትዮጵያዊያንና አፍሪካውያን እጅግ ከሚጸየፉት የቅኝ ግዛት አመለካከት ያልተላቀቀ መሆኑ ኢትዮጵያውያንና በአጠቃላይ የአፍሪካ ሕዝቦች እንዲጠሉትና እንዲጸየፉት የሚያደርግ መሆኑን ማስታወስ አለበት፡፡

እጅግ ደም የሚያፈላው ንቀቱ ደግሞ የአፍሪካ አገሮች በጉዳያቸው ላይ የሚመክሩበትን የአፍሪካ ህብረት የመሪዎችን ጉባኤ "የኮክቴል ፓርቲ" ብሎ መጥራቱ ነው ። ልብ በሉ ከአውሮፓ ውጭ ያሉ ሕዝቦች  ላይ የዚህ አይነት ንቀት ያለው ሰው ነው ለኢትዮጵያውያን የሰብአዊ ምብትና ሃሳብን የመግለፅ ነፃነት ተቆርቋሪ ሆኖ ለመቅረብ የሚዳዳው።

በዚህ የተንደረደረው ሹ·ብዬ ስለአውሮፓውያን የበላይነት በሌሎች አገሮች ላይ ሊኖራቸው ስለሚገባቸው አዛኝ ናዛኝነት ወደ ማተት ተሸጋገረ፡፡

“እንደሚመስለኝ ምዕራቡ ዓለም ኢትዮጵያ ላይ ጫና ለማድረግ እንደዚህ ያሉትን ስብሰባዎች (የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ) በነፃ ፕሬስ ላይ አቋሙን ለማሳወቅና ለታሰሩ ጋዜጠኞች ድጋፍ ለመስጠት የተፈጠረለት ዕድል አድርጎ ሊጠቀምበት ይገባል፣ ጋዜጠኞች ታስረው በኮክቴል ፓርቲ ላይ መገኘት እንደማይገባ ለዲፕሎማሲው አለም ማሳወቅ አለባቸው” ብሎናል።

ሹ·ብዬ “ምዕራባውያን ለኢትዮጵያ ሉአላዊነት ዋጋ ሳትሰጡ በምትፈልጉበት መንገድ ለመንዳት እጇን ጠምዝዙ” እያለ ነው፡፡ ሹ·ብዬና ከቅኝ አገዛዝ አመለካከተ ያልጸዱት መሰሎቹ አንድ ማወቅ ያለባቸው ነገር፣ ኢትዮጳያ በሉአላዊነቷ ጉዳይ ላይ የማንንም ጣልቃ ገብነት ፈቅዳ የማታውቅ፣ ለወደፊትም የማትፈቅድ መሆኑን ነው፡፡

አሜሪካም ሆነች አውሮፓወያን ይህን ጠንቅቀው ያውቂታል፡፡ ይህን የማያውቀው ምናልባት ፈረንጆች በአፍሪካውያን ላይ የበላይነት ያላቸው የሚመስለው ሹ·ብዬ ብቻ ይመስለኛል፡፡

ሹ·ብዬ ፈረንጅ ወገኖቹ የኢትዮጵያን እጅ እንዲጠመዝዙ ለመቀሰቀስ ያነሳሳው “ኢትዮጵያ ውስጥ ጋዜጠኞች ታስረዋል” የሚለው ኢትዮጵያዊያንን ያሰለቸ ወሬ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ስራቸው ጋዜጠኝነት የሆነው ጓደኞቹ ያላቸው ሰዎች በጋዜጠኝነታቸው በሰሩት ስራ ክስ እንዳልተመሰረተባቸው ይታወቃል፡፡

የተከሰሱት በሽብርተኝነት ወንጀለ ነው - የሽብረተኞችን ዓላማ ለማስፈጸም ተባብረው በመንቀሳቀሳቸው፡፡ ጥፋተኛ ለመባል ያበቃቸው ፍርድ ቤት የቀረበባቸው ማስረጃም፣ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሽብርተኝነት ከተፈረጀ ቡድኖች ጋር በመገናኘት የሽብር ተግባር ለመፈፀም በማሴር ነው።

ሹ·ብዬ ራሱ ኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰሰውና ጥፋተኝነቱ በማስረጃ ተረጋግጦ ቅጣት የተወሰነበት በጋዜጠኝነት በሰራው ስራ አይደለም። ይህን ሹ·ብዬም ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡ አብነግ ከተባለው አሸባሪ ቡድን ጋር በመስማማት ዓላማውን ለማስፋፋት በመተባባር የኢትዮጵያን ድንበር ጥሶ በመግባቱ ነው። ሸብዬ ከአሸባሪ ቡድን ጋር ለመስራት

ወደኢትዮጳያ ቢገባም በአሸባሪነት ወንጀል ጥፋተኛ አልተባለም። በህገወጥ መንገድ የኢትዮጵያን ሉአላዊ ድንበር ጥሶ በመግባና ከሽብርተኞች ጋር በመተባባር ወንጀል እንጂ።

ኢትዮጵያ ሉአላዊት አገር ነች፣ ማንም ፍቃድ ሳያገኝ እንደባለጌ ቤት ዘው ብሎ የሚገባበት አገር አይደለችም። ይሕዝቧን ዘላቂ ሰላምና ልማት ለማረጋጋጥ በሕዝቦቿ ውሳኔ ሕገ መንግስት ቀርጻ ከዚህ ሕገመንግስት የመነጩ ሌሎች ሕጎችን አውጥታ የምትተዳደር ሉአላዊ አገረ ነች፡፡ ሹብዬ ለወደፊት ስለኢትዮጵያ ለማውራት አፉን ከመክፈቱ በፊት ይህን ሊያስታውስ ይገባዋል።

ሹብዬ አሸባሪ ተብሎ ከተፈረጀ ቡድን ጋር ጀማ መስርቶ የተያዘው አሜሪካ ውይም አውሮፓዊቷ እንግሊዝ ወይም የራሱ አገር ስዊድን ውስጥ ቢሆን ኖሮ በአሸባሪነት ወይም ከአሸባሪ ጋር በመተባበር ወንጀል ይጠየቅ እንደነበር አያውቅ ይሆን? እኛ ኢትዮጵያውያን ግን ይህን እናውቃለን።

ወይንስ ኦብነግ አሸባሪ አይደለም እያለን ነው? ኦበነግ አሸባሪ አደለም እያለን ከሆነ አሜሪካ በአሸባሪነት የፈረጀችው የአልቃይዳ የአፈሪካ ክንፍ አልሸባብ አሸባሪ አይደለም እያለ መሆኑም ሊሰተዋል ይገባል፡፡ ምክንያቱም ኦብነግ በኢትዮጵያ የአልቃይዳ አልሸባብ ተልዕኮ አስፈጻሚ ነውና፡፡

በቅርቡ በቦስተን ማራቶን ፈንጂ አፈንድተዋል ተብለው ተጠርጥሮ ሲፈለግ የነበረውን ወጣት ከመያዙ በፊት አግኝቶት ጥቆማ ሳያደርግ ቀርቷል የተባለ ሮቤል የተባለ ወጣት በዚህ ድርጊቱ ብቻ የወንጀል ተባባሪ ተብሎ መጠየቁን ሹብዬ ያወቃል ብዬ እገምታለሁ፡፡

እንግዲያው በኦበነግ መሪነት የኢትዮጵያን ድንበር ጥሶ የገባው ሹብዬና በማንኛውም መንግድ ሽብርን ጨምሮ ሕገመንግስታዊውን ስርአት በሃይል እንዳለሁ ብሎ በይፋ ከለፈፈው ግንቦት ሰባት ከተባለ ቡድን ጋር የተባበሩት ጓደኞቹ ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ሽብርተኝነትን በመተባበር ወንጀል የማይጠየቁበት ምክንያት ምንድነው?

እንግዲህ በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ያለው ማርቲን ሹብዬ የተባለው ስዊድናዊ ነው ሰሞኑን የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሃላፊ ጆን ኬሪ “የኮክቴል ፓረቲ” የሚለው አፍሪካውያን የአፍሪካ ሕብረት 50ኛ ዓመት ክብረ በኣል ስብሰባ ላይ እንዳትገኙ፣

አውሮፓውያን የኢትዮጵያን እጅ ጠምዝዙልኝ ሲል የተማጸነው፡፡ እኛ ኢትዮጵያዊያን ደግሞ ገና ከቅኝ ግዛት አመለካካት ያልተላቀቀ ጋዜጠኛ ብለነዋል፡፡